# አቶ ፀጋይ በርሀ የትግራይ ክልል ፕረዚዳንት ባለፈው ሳምንት ለኢትዮጵያን ፎሮም ፖሊቲካል ስቪሊቲ ፓል ቶክ ሩም ስለሰጡት ቃለምልልስ የተሰጠ አስተያየት

ይኩኖ መስፍን
ቦስቶን
11/29/2007

በመጀመርያ ቃለምልልሱ በአማርኛ ቋንቋ ስለነበረ እኔም በተቻለኝ መጠን ሀሳቤን በአማርኛ ለመግለፅ እሞክራለሁ::

አቶ ፀጋይ በርሀ ትግራይ ክልልን በሚመለከት በርከት ያሉ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጠያቄዎች የቀረበላቸው ሲሆን በሰጡት መልስ ዙርያ ግን ቡዙ አጠያያቂና አወዛጋቢ መስሎ ስለታየኝ ለውይይት ይጠቅማሉ በማለት ዋና ዋናዎቹን በመዳሰስ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ::

በአገራችን  የሚፈልገውን የዲሞክራሲ፣ የኢኮኖሚና የፖሊቲካ እድገት እግቡ ላይ እንዲደርስ በሚደረገው ትግል ተቀዋሚዎችም ሆኑ የመንግስት አካላት ሃላፊነት የጎደለው ድርጊት እንዳይፈፅሙና ለዲሞክራሲ ግንባታ የተከፈለውን መስዋእትነት እንዲያስታውሱ የበኩላቸውን ዜግነታዊ ሃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ይጠበቅባቸዋል::

እንደሚታወቅውና በተደጋጋሚ እንደተገለፀው ህወሓት/ኢህአዴግ ደርግን ለማስወገድ ባደረገው ከፍተኛ ተጋድሎ አገራችን ኢትዮጵያን እያደማና በግፍ እየጨፈጨፈ የነበረው ነብሰ ገዳይ ደረግ/ኢሰፓ አስወግዶ ባገራችን የልማትና የዲሞክራሲ ጭላንጭል እንዲታይ አድረጓል::

ሆኖም ግን ይህን ከፍተኛ መስዋእትነት የተከፈለበትን የህዝብ ጥያቄ እንደተፈለገውና እንደታለመለት ሊሄድ አልቻለም:: ይህም እሰካሁን እየታየ ያለው ችግር ሁለቱም ተቃዋሚዎችና ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ልዩነታቸውን በማቻቻል ነፃና ግልፅ የሆነ አገራዊ ጉዳይና መሰረታዊ የአገር ቋሚ ጥቅም ከማስቀደም ይልቅ የየራሳቸውን የስልጣን ኮረቻ ሲያመቻቹና ለስልጣን አንተ ወያኔ አንተ ሻዕብያ ሲባባሉ መታዘባችን በጣም የሚያሳዝን ነው::

አቶ ፀጋይ በረሀ የህወሓት ከፍተኛ ባለስልጣንና የትግራይ ክልል አስተዳዳሪ እንደመሆናቸው መጠን ዜጎች ከሳቸው የሚጠብቁት ለዲሞክረሲ እድገት፣ ለሰላም መስፈንና አጠቃላይ ትክክለኛ ፍትህ ለሁሉም እንዲዳረስ የበኩላቸውን ጥረት ሲያደርጉና የታገሉለትን አላማ ከሌሎች እሳቸውን ከሚቃወሙ ሃይሎች በነፃ ትወዳድሮው ሲያሸንፉና በህዝቦች ሙሉ ተቀባይነት አግኝቶው ሲሾሙ ነው የትግሉ አላማ ግቡ መታ የሚባለው:: ይህ መሰረታዊ የህዝብ ፍላጎት እስካሁን በትክክል በተግባር ሲተረጎም አልታየም:: ባለፈው ሳምንት አቶ ፀጋይ ለኢትዮጵያን ፎሮም ፖሊቲካል ሲቪሊቲ ሩም የሚባለው በኢህአዴግ ደጋፊዎች ስብስብ የሚመራ ፓል

ቶክ ሩም ቀርበው በተደረገላቸው ቃለ ምልልስ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ይመስል ነበር::
መጀመርያ የቀረበላቸው ጥያቄ ስለ ትግራይ የትምህርት፣ የመንገድ፣ አጠቃላይ ኢኮኖሚ እንዲሁም ስለ አድዋ ከተማ ወደቿላ የመቅረትና ሌሎችም ያካተተ ሲሆን አቶ ፀጋይ እነዚን ጠያቄዎች በሚመለከት ሰፋ አድርገው መልሰዋል:: በተለይ በኢኮኖሚ ረገድ ትግራይ በጥሩ ሁኔታ እንዳለችና ህዝቡም ደስተኛ እንደሆነ ህዝቡ የሚፈልጋቸውና የሚጠይቃቸው እየተሟሉለትና እየተስተካካሉ እንደሆነ አብራርተዋል:: በትምህርትም ደረጃ ዛሬ ከማንኛውም ግዜ በላይ የተማሪ ቁጥር እየጨመረ እንደሆነና በጥሩ ሁኔታ እንዳለን አስረድተዋል:: በትግርኛ ቋንቋ ጥራት ግን ብዙ እንደሚቅርና ተባብሮ መስራትና መረዳዳት እንደሚያስፈልግ ሳይገልፁ አላላፉም::

ቀጥሎ የቀረበው ጥያቄ  በቅርቡ በትግራይ ክልል እንዲቀሳቀስ የህግ ፍቃድ ያገኘው ዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ሉአላዊነት የተባለው የፖሊቲካ ፓርቲ አሰመልክቶ የትግራይ ህዝብ እንዴት ያየዋል የሚል ነበር::
ለዚህ ጥያቄ አቶ ፀጋይ ሲመልሱ የትግራይን ህዝብ እጅግ አሳዝኖታል ብሏል:: እነ አቶ ገብሩ ተቀባይነት እናገኝበታለን ብለው የአሰብን ወደብ ማንሳታቸውና መጠየቃቸው ህዝቡን በጣም አሳዝኖታል:: እሱ ብቻ ሳይሆን ይዘውት የመጡ ስምም ዓረና የሚለው መያዛቸው ሆን ብለው የትግራይን ህዝብ እንዲከፋፍሉ ነው:: ስሙ የቀዳማይ ወያነ ስም በመሆኑ የተወሰነ አካባቢ ለመያዝና ለማደናገር ነው ብለዋል::

በመጀመርያ ደረጃ አቶ ፀጋይ በርሀ እያስተዳደርኩት ነው የሚሉት የትግራይ ህዝብ ብዛት በግምት ከ4.5---5 ሚልዮን እንደሚሆን ነግረውናል:: ይህል ያህል ህዝብ እነ አቶ ገብሩ አሰብን በህግና በሰላማዊ አግባብ እናስመልሰዋለን በማለታቸው እንዳሳዘነው በምን አወቁ? የትግራይ ህዝብ የአሰብ ወደብ በሰላም የሚያገኝበት መንገድ አለ ከተባለ ለምን ያዝናል:: ወደብ አያስፈልገውም ማለትዎ ይሆን? እኔ እስከገባኝ ድረስ ባድመ፣ ፀረና፣ ኢሮብ እና ሌሎች ጥንታዊ የኢትዮጵያ ግዛቶች ለልማታችንና ለሰላማችን ስንል ይቅርብህ እየተባለ አይደለም ያለው:: ስለዚህ አቶ ፀጋይ የትግራይ ህዝብ መቸ ተጠይቆ መቸ መልስ እንደሰጠ ቢነግሩን ጥሩ ነበር::

በዚህ በጣም አጭር ግዜ ውስጥ እሳቸውም በስብሰባ ተወጥረው ባሉበት ግዜ የአምስት ሚልዮን ህዝብ ፍላጎት ይህ ነው ብሎ መናገር በጣም ስህተት ነው:: ፍለጎታቸው ምን እንደሆነም ከወዲሁ ያስታውቃል:: በኔ እምነት እነ አቶ ገብሩ አስራት የቀዳማይ ወያነ ብቻ ሳይሆኑ የህወሓትም ናቸው ነበሩም:: እንዲያውም በከፍተኛ አመራር የነበሩ ሰዎች በመሆናቸው እነሱ ከህወሓት ከመውጣታቸው በፊት የተደረገው ሁሉ ከተጠያቂነቱም አያመልጡም:: ስለዚ እንኳንስ ዓረና ሌላም ቢሉ ችግር ያለው አይመስለኝም ዋናው ከያዙት መሰረተ ሃሳቡ ላይ ነው መከራረርና መታገል ሚያስፈልገው:: በአግባቡ የሚቃወመን ድርጅት ብናገኝ ግማሽ መንገድ ሂደን እንቀበለዋለን እየተባለ ሲነገረን እንዳልነበረ ሁሉ አሁን ህጋዊና ሰላማዊ መንገድ ተከትሎ የተለየ ሃሳብ ላቀረበ የከፋውን ስም መስጠት ምን ያህል ለዲሞክራሲ የቆማቹ እንደሆነ ያሳያል::

ሆን ብለው ህዝብን ሊከፋፍሉ ነው ለሚለው? እዚህ ላይ ህዝቡ ራሱ ትከፋፍሉናላቹ ይበል:: እድሉ ይሰጣቸውና በአግባቡ እንዲንቀሳቀሱ ሁኔታዎች ይመቻቹ:: ህግና ስርአት ባለው መንገድ አለን ሚሉትን ሃሳብ ወደ ህዝቡ እንዲያቀርቡና አማራጭ ሃሳበቸው ለህዝብ እንዲያዳርሱ መንግስት የህዝብ መገናኛ ብዙሃን እንዲጠቀሙ ይፍቀድ:: በነፃ የመንቀሳቀስ መብታቸው ተጠብቆ ህዝብን የመሰብሰብና የማደራጀት ስራቸው በህጉ መሰረት እንዲያካሂዱ ይፈቀድ:: ከዛ በሓላ ነው ህዝብ ምን እንዳለ ማውቅ የሚቻለው አቶ ፀጋይ?

ሌላው ስለ ቅንጅት ከሻዕብያና ከኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር አብሮ መስራት ጉዳይ እንዴት ያዩታል ተብለው አቶ ፀጋይ ሲጠየቁ በቀጥታ ኤሰጡት መልስ አሁንም በእነ አቶ ገብሩ ነው::

እነ አቶ ገብሩም እኮ ያው ናቸው::ቅንጅት ናቸው:: እኛ የያዝነው ጎደና ትክክለኛው ጎደና ነው:: ለዚህ ትክክለኛ ጎደና ሻዕብያ እየተቃወመን ነው:: ቅንጀት እየተቃወመን ነው:: እነገብሩም እየተቃወሙን ነው:: ስለዚህ ሁሉም አንድ ናቸው::

ይህንን አባባል የተለመደና አሁንም እየቀጠለ ያለ ፀረዲሞክራሲ አስተሳሰብ ይመስለኛል:: ድርጅቶቹም ሆኑ ግለሰቦች ባለቸው የፖሊቲካ ፕሮግራም ሊመዘኑ ይገባል እንጂ ለተቃዋሚ ሁሉ ሻዕብያ የሚል ስም እየለጠፍክ የተቃዋሚዎችህን ስም ማጥፋት ከህግ ውጭ ብቻ ሳይሆን ፀረ ዲሞክራሲ፣ ፀረ ሰላምና ፀረ ፍትህም ነው:: እውነት አቶ ፀጋይ ለዲሞክራሲና ለሰላም የሚታገሉ ከሆነ እነሆ ሜዳው ያሳዩን ባይሆንማ እነ አቶ ገብሩ ከመቸ ወዲህ ነው ከሻእብያ ጋር የተሞዳሞዱት…? እርስዎስ እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ አቶ መለስን ተቃውሞው ከነ አቶ ገብሩ ጋር ሻዕብያ ለአንዴና ለመጨረሻ እናጥፋው በሚለው ወገን አልነበሩም እንዴ? ለመሆኑ ሃሳባቸው ለምን እንደቀየሩ የሚያውቅ ስው ይኖራል? ቢነግሩንስ? የአቶ ገብሩ አሰራት ምክትል እንደነበሩ ሁላችን እናውቃለን በዚህ የስልጣን ዘመናቹ የሚያውቁት ሚስጢር ካለ ቢያካፍሉን ምንአለበት? ምክንያቱም ለአቶ አብርሃም መልስዎ ሲሰጡ እነ አቶ ገብሩ ስለ ኤርትራ ለሚጠይቅና ለሚከራከር ይኮረኩሙ ነበር በኋል:: ዘርዘር አድርገው ቢገልፁልን ለሁላችን ጠቃሚ ይሆን ነበር::

ከዚህ ርእስ ሳንወጣ አቶ ፀጋይ ለጠያቂያቸው ሲያብራሩ እነ ገብሩ እኮ አጠቃላይ ትግሉን ስህተት ነበር በለው እንድያውም ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ይቅርታ ጠይቀዋል ሲሉ ለአድማጮቻቸው በግልፅ ተናግሯል::

ውሸት ሲደጋገም ሀቅ ይመስላል እንደሚባለው ሁሉ ማንኛውም አይነት ድርጅት ሆነ ግለሰብ በአቋሙና በእምነቱ ለህዝብ እና ላገር የማይጠቅም መሆኑ ማሳየትና ማስገንዘብ ሲሳነን ባልተባለና በሌለ ህዝብን ማደናገር አሁንም ህዝቡ ይታዘቦታል እንጂ ትርፍ አያስገኝልዎትም:: የሚያዳምጣቸው ህዝብ የተለያየ መገናኛ ብዙሃን የማግኘት እድል (አክሰስ) ያለው በመሆኑ፣ ከድምፂ ወያነና ጋዜጣ ወይን ውጭም እንደሚያገኝ ስተውት ይሆን:: ወይስ አድማጫቸው ትግራይ ውስጥ ያለ መሰላቸው? እንጂ አቶ ገብሩ በዚህ ጉዳይ የተናገሩት ሃቁን ለመናገር ቢፈለግ ኑሮ ስለ ኢትዮ --- ኤርትራ ድምበር ውሳኔ የተሰጠውን ፍርደ ገምደል ውሳኔ ለመቃወም የተጠራው

ሰላማዊ ሰልፍ አቶ ገብሩ ተጋብዘው ሲናገሩ ያሉት *እኛ የአልጀርስ ስምምነት ሲፈረም የመንግሱቱ አካል ስለነበርን በዛው ሰአት አለመቃወማችን እኛም ተጠያቂዎች ነን:: ለዚሁ በዚህ አጋጣሚ ለኢትዮጵያ ህዝብ ይቅርታ እንጠይቃለን ነው ያሉት::* ይህን መሆኑ እየታወቀ ትግሉን ስህተት ነበር ብለዋል ብሎ በድፍረት መናገሩ ህዝብን ማሳሳት ይመስላል:: እውነት በዚ ጉዳይ መናገር ቢፈልጉ ኑሮ አቶ ስብሃት ነጋ ለድምፅ ወያነ ሬድዮ በሰጡት ቃለምልልስ ኤርትራ አሁን ከውስጥም ከውጨም ብትነካ እጅና እግራችን አጣጥፈን አናይም በለው ነበር:: ስለዚህ ምን አስተያየት ነበሮት:: ምንስ ይላሉ? መነሳት የነበረበት ይህንን ነበር::

አቶ ፀጋይ ሻዕብያ የሁለችን ጠላት ነው:: ሻዕብያ ኢትዮጵያዊ ሊሆን አይችልም:: ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሌተቀን እየሰራ ያለ የሁላችን ኢትዮጵያውያን ጠላት ነው አስመራ ውስጥ ከሚገኙት ጥቂት ከሃዲ ቅጥረኞች በስተቀር:: ቅንጅት የእርሶ መንግስት ህጋዊ ፍቃድ ሰጥቶ በአገራዊ ፖሊቲካዊ ጉዳይ በቴሌቪዥንና በሬድዮ ተከራክሮ በኢትዮጵያውነቱ መንግስት የሚጠይቀውን ሁሉ አሟልቶ በመቅረብ በአገራችን ካሉት ታላላቅ ከተሞች ኢህአዴግን በምረጫ 97 አሸንፈዋል:::: በተለይ በአዲስ አበባ፣ ናዝሬት፣ድሬዳዋ፣ባህረዳር ሌሎቹም:: እስከ 90 የሚያህሉ በኢትዮጵያ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ናቸው ስለዚህ እነዚህ ሻዕብያ ሊሆን አይችሉምና ስም ማጥፋቱ ቀርቶ በፕሮግራምና ፖሊሲ ቅንጅትም ሆነ ሌላ ቻሌንጅ መደራረጉ ለርሶም ለሓገራችንም ለተቃዋሚ ፖሊቲካ ፓርቲዎችም ይጠቅማል እላሎህ::

በመጨረሻ አቶ ፀጋይ ሃሳባቸውን ሲያጠቃልሉ ውጭ ያለውም ሆነ ውስጥ አብሮ መስራት እንዳለበትና ተባብረን ችግሮቻችንን ማሸነፍ እንደሚቻል አስምረውበታል:: ቀጥለውም የእነ አቶ ገብሩ ፓርቲም ቢሆን እዚ አገር አይወራም ጭራሽም አይታወቅም ብለዋል:: ቀደም ብለው የተናገሩት ረስተውት ይሆን? ዓረና የዓሰብን ጉዳይ በሰላማዊ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ እናስመልሳለን በማለታቸው ህዝቡ አዝኖባቸዋል ብለው ነበር አሁን ደግሞ ጭራሽ አይታወቁም ሰውም በዚ ጉዳይ አያወራም ብለዋል:: ፍርዱ ለአንባቢ እተወዋሎህ::
እሳቸው ብቻ አይደሉም የፓልቶኩ ባለቤትም አብርሃም/አባማላም ክቡር ፕረዚዳንት አሁን የሚባለው ፓርቲ እዚ አገር ስሙም አይታወቅም በማለት ቃለምልልሱ አብቅቷል::

ዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ሉአላዊነት ከመንግስት ፍቃድ ማግኘቱና መመስረቱ ይፋ የሆነው በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ በሪፖርተር ጋዜጣ፣ በአመሪካ ድምፅ ራድዮ አማርኛ ፕሮገራምና ትግርኛ፣ በጀርመን ድምፅ ራድዮና በዓይጋ ፎሮም ከሪፖርተር ጋዝጣ የተወሰደ ዘገባ ወጥቶ ነበር እንግዲህ አባማላም የትኛው ሚድያ እንደሚከታተልና እንደሚሰማ ምንም ባናውቅም ፓርቲው እንደተመሰረተ በውል እያወቀ እየተከራከረበት እያለ አይታወቅም ማለቱ ትርፉ ተእዝብት ነው::

በመጨረሻ የጋራ ጠላታችን ድህነት፣ በሽታ፣ ጦርነት በጋራ ለማጠፋትና ለመመከት ከተፈለገ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሚያቀርበው የተለያየ መፍተሂ ሓሳብ የማቅረብ መብቱ በህግ የተጠበቀ ሆኖ ልዩነቶች የማስተናገድ ልምድ እና ባህል ካላዳበርን ዲሞክራሲ በምንም አይነት መንገድ ሊመጣ አይችልም:: አገራችን ኢትዮጵያ ከነዚ

መሰረታዊ ችግሮች ተላቃ የሰላም፣ የፍትህና የዲሞክረሲ አብነት እንድትሆን በመጀመርያ የተለያዩ የፖሊቲካ ፓርቲዎች የአገራችን ህገመንግስት በሚፈቅደው መሰረት በነፃ የመንቀሳቀስና የመደራጀት መብታቸው ሳይገደብ መንቀሳቀስ ሲችሉ ብቻ ነው። ልዩነት እያንዳንዳችን እጥረቶቻችንና ችግሮቻችን የምናይበት መነፅር በመሆኑ የሚቃዎሙትም ሆነ የሚደግፉት በጠላትነት መፈራረጅ ካላበቃ የትም እንደማንደርስ ሁላችን የምናውቀው ጉዳይ ነው። በልማቱም በፖሊቲካውም በማንኛውም አገር አቀፋዊ እንቅስቃሴ ህዝብ በትጋትና በፍቃድ ካልተሳተፈበት የእኛ እናውቅልሃለን ፖሊቲካ መጨረሻው ዲክታቶርያዊ አገዛዝ እንደሚሆን ካለፉት ገኾሮዎቻችን ያየነውና የተረዳነው ሃቅ ነው። ስለሆነም ልዩነቶቻችንን ይዘን ለጋራ ጥቅማችንና ለመሰረታዊ ቋሚ ያገራችን ጥቅም ለማስከበር ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ ፖሊቲካዊ ትግል ተቀብለን ሰላማችንና ልማታችን ማፋጠን አለብን እላለሁ።